

54-1

# ተጠንቀቁ!

## ጤናማ ያልሆነ ፍርሃት እርምጃን ያደናቅፋል

"ቆራጥነትና ድፍረት ይኑራችሁ፤ ከእነርሱም የተነሳ ከቶ አትፍሩ፤ አትደንግጡም፤ ምክንያቱም ራሱ አምላካችሁ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሆናል፤ አይጥላችሁም፤ አይለያችሁም" (ዘዳግም 31፥6)።

ፍርሃት መንፈሳዊ እርምጃችንን ብቻ የሚያደናቅፍ ሳይሆን፥ ዕለታዊ ኑሮአችንንም ጨለማ ያደርጋል። ፍርሃት ትንሹን ትልቅ፥ ደካማውን ብርቱ፥ የሌለውን እንዳለ፥ የሩቁን ቅርብ አድርጎ ያሳያል። ፍርሃት የሰው አዕምሮ በትክክለኛው እንዳያስብ ቀልፎ ይይዛል፤ ብልጡን ሞኝ፣ ብርቱውን ደካማ ያደርጋል። ከዚህ በታች ያቀረብንላችሁ ታሪክ ቀልድ ይምሰል እንጂ ፍርሃት በሰው ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ጥሩ አድርጎ ያሳየናል። ስፔን አገር ባርሴሎና በሚባል ከተማ ውስጥ አንድ ጊዜ አንድ ሰው ትልቅ ትሬንታ እየነዳ በአንድ ከከተማ ወጣ ባለ መንገድ ላይ ይሄድ ነበር። አንድ ገበሬ ከመንገዱ ዳር ቆሞ ያንን ባለመኪና እንዲወስደው ጠየቀው። ሾፌሩም የሰውየውን ጥያቄ ተቀበለና ከዕቃ መጫኛው ላይ አሳፈረው። ወዲያው ዝናብ መዝነብ ሲጀምር ያ ሰው ከዝናቡ ራሱን የሚሸፍንበት ብልሃት ሲፈልግ፥ አንድ የሬሳ ሳጥን ተጭኖ አየ። ባዶ መሆኑን አይቶ የሬሳ ሳጥኑ ውስጥ ገብቶ ተኛ፤ አጋጣሚ ሆኖ እንቅልፍ ወሰደው። በዚህ መካከል ሁለት ሌሎች ሰዎች መንገድ ላይ ቆመው ባለ ትሬንታውን እንዲያሳፍራቸው ጠየቁት። ሾፌሩም ቀደም ሲል ገበሬው ከተሳፈረበት የዕቃ መጫኛ ላይ እነርሱንም አሳፈራቸው። እነዚያ ሁለት ሰዎች አካባቢያቸውን በዓይናቸው ሲቃኙ የሬሳ ሳጥን እንዳለ ተመለከቱ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ያ ገበሬ ከእንቅልፉ ሲነቃ፣ የሬሳ ሳጥኑን ከፈት አድርጎ ዝናቡ መዝነቡን አቁሞ እንደሆነ ለማየት ከሬሳ ሳጥኑ ውስጥ ራሱን ብቅ አደረገ። እነዚያ ሁለት ሰዎች "የሞተ ሰው ተነሳ" ብለው ይሆናል በፍርሃትና በድንጋጤም ተሞልተው በኃይል ከሚበረው መኪና ዘለው ሲወርዱ፥ አንደኛው ከባድ አደጋ ሲደርስበት፥ ሁለተኛው ሰው ወዲያውኑ ሞተ። ነገሩ የሚያስቅ ቢመስልም ጤናማ ያልሆነ ፍርሃት በሰው ሕይወት ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት በመጠኑም ቢሆን ያሳያል።

"ባይሳካልኝስ?...ተቀባይነት ባላገኝስ?...ሰዎች ቢጎዱኝስ?..." የሚል ፍርሃት አለብን። "ሰዎች ስለ እኔ ምን ይሉ፣ ያስቡ ይሆን?..." የሚለው ሌላው ፍርሃታችን ነው። ፍርሃት ደስታና ሰላማችንን የሚገፍ ብቻ ሳይሆን፥ በሕይወታችን ምንም ዓይነት እርምጃና ውሳኔ እንዳናደርግ አዕምሮአችንን የሚዘጋ ብርቱ ኃይል ነው። "ፍርሃት" ለሰው ልጅ በዙሪያው ያለን ብርሃን በማሳየት ፈንታ፥ ጨለማውን አተልቆና አሳድጎ በማሳየት ሊያገኘው የሚችለውን ምድራዊም ሆነ ሰማያዊውን በረከት እንዳያገኝ ያደርገዋል። ይህንንም ሙሴ የከነአንን ምድር እንዲሰልሉ በላካቸው በአሥራ ሁለቱ ሰላዮች የሕይወት ልምምድ ውስጥ እናያለን። በእግዚአብሔር በመታመን ደፋር የነበሩት ኢያሱና ካሌብ የስለላ ተግባራቸውን ጨርሰው ሪፖርት ሲሰጡ፥ "በአገሪቱ ላይ አሁኑኑ አደጋ በመጣል እንውረሳት፤ምክንያቱም እነርሱን ድል ለመንሳትየሚያስችል በቂ ኃይል አለን" አሉ (ዘሁልቁ 13፥30)። የተቀሩት አሥሩ ሰላዮች ግን በፍርሃት እየተንቀጠቀጡ፥ "እኛ በእነርሱ ላይ አደጋ ለመጣል ከቶ ኃይል የለንም፥ በዚያ የሚኖሩት ሕዝብ ከእኛ ይበልጥ ብርቱዎች ናቸው…ቁመተ ረዣዥሞች የሆኑ ጠረኞች ናቸው፤ በዚያም ግዙፋን የሆኑትን የዓናቅን ዝርያዎች አይተናል፤ እኛ በእነርሱ ፊት ልክ እንደ ፌንጣ ያህል ሆነን ነበር የታየነው፤ እነርሱም እንደዚያው አድርገው ሳይመለከቱን አይቀሩም" (ዘሁልቁ 13፥31-33) በማለት ራሳቸው ፍርሃት ተረብሸው ሕዝቡንም አስረበሹት። ለዚያም ዋጋ ከፍለውበታል።

## 1. የፍርሃት ዓይነቶች

### ሀ. ጤናማ የሆነ ፍርሃት

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው በውስጡ ካኖራቸው ስሜቶች መካከል አንደኛው “ፍርሃት” ነው። ፍርሃት በሰው ሕይወት ጠቃሚ ባይሆን ኖሮ እግዚአብሔር ፍርሃት እንዳይሰማው አድርጎ ይፈጥረው ነበር። አዋቂዎች ሲናገሩ ሰውን ወቅታዊ የሆነ ውሳኔ እንዲያስተላልፍ የሚያደርጉት አራት ዋና ዋና ነገሮች ሲሆኑ፥ እነርሱም ፍርሃት፣ ተስፋ፣ እምነትና ፍቅር ናቸው፤ ከእነዚህ መካከል ትልቁ ፍርሃት ነው ይላሉ። ጤናማ ወይንም ትክክለኛ የሆነ ፍርሃት ከአደጋ እንድንሸሽ ያደርገናል። ለምሳሌ፥ መንገድ ስናቋርጥ ትልቁ ፍርሃታችን በመኪና እንዳንገጭ ነው። መፍራታችን አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንድናደርግ ይረዳናል። በውስጣችን የፍርሃት ስሜት ባይኖር ኖሮ እየበረረ ከሚመጣ መኪና ጋር መጋጨት በቻልን ነበር። ፍርሃት አንዳንድ የተፈጥሮ ህጎችን በሕይወታችን እንድናከብር ያደርገናል። እነዚያን የተፈጥሮ ሕጎችን ስንሰብር ያልጠበቅነው መጥፎ ነገር ይደርስብናል ብለን ብንፈራ፥ ፍርሃታችን አግባብ ያለው ወይንም ጤናማ ፍርሃት ነው። ሕግ ካልጣስን በአካባቢያችን ፖሊስ ማየቱ አያስፈራንም። ከጋብቻ ክልል ውጪ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ካልፈጸምንና እንዲሁም ኤይድስ ሊያስተላልፉ ይችላሉ ከሚባሉት ነገሮች ከተጠነቀቅን፥ “ኤይድስ ይይዘኝ ይሆን?” ብሎ መፍራት ከአግባብ ውጪ ነው። ገንዘባችንን በአግባቡ በአቅማችን ከተጠቀምንበት የገንዘብ ማጣት አያስፈራንም።

### ለ. በእውነት ላይ ያልተመሠረተ ፍርሃት

በእውነት ላይ ባልተመሠረተ ምናልባትም ፈጽሞ በማይደርስ ነገር አዕምሮአችን ሲሞላ የማሰብ ችሎታችንን ፈጽሞ ሰንካላ የሚያደርገው መጥፎ ስሜት ነው። “ያ ቢደርስብኝስ”… ያ ቢፈጸምብኝስ?...ትዳሬ ቢፈርስስ? የምወደው እከሌ ቢሞትብኝስ? ከሥራ ብወጣስ?” በማለት ገና ባልደረሰበት ነገር የሚጨነቅ ሰው ጤናማ የሆነ የሕይወት እርምጃ ሊኖረው አይችልም። ለምርመራ ሀኪም ቤት ሲሄድ ፍርሃቱ “በሽታ ይገኝብኝ ይሆን?” የሚል ነው። በሽታ ከተገኘበት ደግሞ ፍርሃቱ ይቀጥልና “የማይድን በሽታ ይሆን?” የሚል ይሆናል። በዚህ አያቆምም፤ ይቀጥልና “እርዳታ በማጣት እሞት ይሆን? ከሞትኩስ ለቤተሰቤ ማን ይጠንቀቃል?” የሚል ፍርሃት ይመጣበታል። “ፍርሃት” በዚህ መልክ ሌላ ትልቅ ፍርሃትን ይወልዳል። አንዳንድ ሰዎች በዜና ማሰራጫዎች ስለ አይሮፕላን ጠለፋ ወይንም አደጋ ከሰሙ ተመሳሳይ እጣ ያጋጥመናል ብለው በመፍራት ጉዟቸውን የሚሰርዙ ወይንም በሌላ የመጓጓዣ ዓይነት የሚጠቀሙ አሉ። ብዙ ሰዎች ቁጥር በሌለው ዓይነት ፍርሃት የተያዙ በመሆናቸው፥ የሥነ አዕምሮ ሊቃውንት ከፍርሃታቸው ለማላቀቅ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ። ይህን ዓይነቱ ፍርሃት ለአማኝ መሠረታዊ የሆነውን የእግዚአብሔር ፍቅርና ኃይል በሕይወቱ እንዲጠራጠር ስለሚያደርገው መንፈሳዊ እርምጃውን ወደ ኋላ ይጎትትበታል። በሕይወታቸው ዓላማ ቢስ የሆኑ፥ እግዚአብሔር የተዋቸው የመሰላቸው የወደፊቱ ጨለማ ሆኖ የሚታያቸው ቢሞቱ እግዚአብሔር መንግሥት ሰማይ እንዳይገቡ የሚከለክላቸው መስሎ ስለሚሰማቸው በፍርሃት ውስጥ የሚኖሩ አሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ “ፍርሃቴ መንግሥተ ሰማይ አልገባም ብዬ አይደለም ፍርሃቴ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ በህይወቴ ምን ያገጥመኝ ይሆን? የሚል ነው” ይላሉ። የፍርሃት ተቃራኒ ድፍረት ነው። “ድፍረት” ማንኛውም ክፉ ነገር ወይንም አደጋ ባለበት ሁኔታ ለማለፍ ሰው በአዕምሮው የሚያስተላልፈው ውሳኔ ነው። “ፍርሃት” ደግሞ ከችግሩ ባሻገር ማየት እንዳይችል አዕምሮውን ዘግቶ የሚያስቀምጠው መጥፎ ስሜት ነው።

## 1. ሰው ለምን ይፈራል?

### ሀ. ውሸት በበዛበት ዓለም በመኖሩ ነው

ሰው በዙሪያው በሄደበትና በደረሰበት ሁሉ ብዙ ውሸቶችን ያያል፣ ይሰማል። ተማሪው፣ አስተማሪው፣ አስተዳዳሪው፣ ወላጆች፣ ልጆች እኩል ሁሉም ይዋሻሉ። መጋቢው፣ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌው፣ ተራ ምዕመኑም፣ የተማረውም ሆነ ያልተማረው በግል ሕይወቱ ይዋሻል። የውሸታችን መጠንና ጥልቀት ይለያይ እንጂ እኔና እናንተም እንዋሻለን። ነገር ግን ትንሽም ሆነ ትልቅ ውሸት ያው ውሸት ነው። ራሱ እየዋሸ በዙሪያው ያሉት ጠንካራ ክርስቲያን ናቸው የተባሉትም ሰዎች ሲዋሹ በመስማትና በማየት ብዙ የቆየ ሰው፥ መጽሐፍ ቅዱስ “አይዞአችሁ! አትፍሩ በእግዚአብሔር ብቻ ታመኑ” በማለት የሚሰጠውን የተስፋ ቃል መቀበል አይሆንለትም። ምክንያቱም ሰዎች በውሸታቸው ሲያታልሉት፣ ያልሆነው “ሆነ” ሲሉት የገቡለትን ተስፋ ሲክዱት ብዙ ጊዜ ስላየና ስለተለማመደ ነው። በእግዚአብሔር ካልታመነ ደግሞ ከፍርሃት ነጻ መሆን አይችልም።

### ለ. የተስፋውን ቃል አዕምሮው መቀበል ስለሚያቅተው ነው

የምንኖረው ሁሉም በግሉ ታግሎና ለፍቶ ከሚኖርበት ዓለም ውስጥ ነው። ያለልፋት፣ ያለድካም በነጻ ምንም ነገር ይገኛል ብሎ ማመን አይቻልም። መጽሐፍ ቅዱስ በሕይወታችን በእግዚአብሔር ከታመንን በመንገዳችን

*ሁሉ እንደሚመራን፣ የሚያስፈልገንን ሁሉ እንደሚሰጠን ተስፋውን ይነግረናል። ይሁን እንጂ ብዙዎቻችን ይህን መቀበል ያቅተናል። የተስፋውን ቃል ተቀብለን እንደ ቃሉ በመኖር ፈንታ፣ የራሳችን የሆነ ቀዳዳ ለማበጀት እንፈልጋለን። በእግዚአብሔር መታመን ሲያቅተን ደግሞ፣ ያኔ ሕይወታችን ጤናማ ባልሆነ ፍርሃት ይሞላል።*

*ሐ. "እንደጠበቅሁት አይሆንም" ብሎ ስለሚያስብ ነው*

*ፍርሃታቸውን መስመር ለማስያዝ የሚጥሩ ሰዎች፥ ችግራቸው አሁን ያሉበት ሁኔታ አይደለም። ትልቁ ፍርሃታቸው "መጨረሻችን እንደ መጀመሪያችን አይሆንም ይሆናል" የሚል ነው። ተረትም እንኳን ቢሆን መጨረሻው የማያምር ተረት መስማት ደስ አይለንም። "…ከዚህ በኋላ በጤንነትና በሰላም ኖሩ…" የሚል አፈጻጸም ያለው ታሪክ (ተረት) መስማት ደስ ይለናል። የሚያስፈራ ነገር ሲያጋጥመን የሚያሳስበን በወቅቱ ያለው ሁኔታ ሳይሆን፥ የመጨረሻው ሁኔታችን ነው። "ወደፊት ሁሉም ነገር መልካም ይሆናል፡ ብሎ የሚነግረንን ሰው እንፈልጋለን። ያልጠበቁት ነገር በሕይወታቸው ደርሶባቸው ኑሮ የጨለመባቸው ሰዎች "መጨረሻዬ ምን ይመስል ይሆን?" ሲሉ ይጠይቃሉ። መጨረሻቸው እርግጥ ነው መጀመሪያ ከነበሩበት በጣም የተለየ ይሆን ይሆናል፤ ይሁን እንጂ ስለወደፊቱ እያሰቡ በመጨነቅ የተቀረውን ዘማናቸውን ደስታ የራቀውና አሳዛኝ ሕይወት ኖረቻቸው ያልፋሉ።*

*መ. የሚያስፈሩ ነገሮች በሞሉበት ዓለም ስለሚኖር ነው*

*ዓለማችን ብዙ መጥፎ ነገሮች የሞሉባት ዓለም ናት። እንዳንፈራ ከሚያደርጉን ነገሮች መካከል አንደኛው በአካባቢያችን ያለውን ሁኔታ አለማወቃችን ነው። ባወቅን ቁጥር ፍርሃታትንም በዚያው መጠን እየጨምረ ይሄዳል። የምንበላውን ምግብ፣ የምንስበውን አየር አጉልቶ በሚያሳይ መነጽር እያየን ቢሆን ኖር፥ ለዓይን ረቂቅ የሆኑ ባክቴሪያዎችንና ልዩ ልዩ ጤናን የሚያቃውሱ ነገሮችን ስለምናይ አንድ ቀን እንኳን ያለ ፍርሃት መኖር አንችልም ነበር። በዓለም ላይ በየጊዜው የሚፈለሰፉትን አጥፊ መሣሪያዎች ብዛታቸውንና አደገኛነታቸውን ብናውቅ ኖር በምድር የምንኖረበት ዘመን አጭር ይሆናል በማለት በፍርሃት የተሞላ ሕይወት ይኖረን ነበር። በ41 ዓመቱ በኬሚስትሪ "የኖቤል ፕራይዝ" ተሸላሚ የሆነው ፕሮፌሰር ሄሮልድ ኡሬይ "እኔ በፍርሃት የተሞላሁ ሰው ነኝ፤ ይህንንም የምጽፈው እናንተም እንደ እኔ እንድትፈሩ ለማድረግ ነው፤ እኔ የማውቃቸው ሳይንቲስቶች ሁሉ ለእናንተና እንዲሁም ለራሳቸው ሕይወት የሚፈሩ ናቸው" ሲል አንድ ጽሁፍ አቀረበ። የእግዚአብሔር ቃል ስለ መጨረሻው ቀን ሲናገር "በዓለም ላይ የሚመጣውን ነገር በመጠባበቅ ሰዎች በፍርሃት ይሸበራሉ" ይላል (ሉቃስ 21፥26)።*

*ዓለም ያለፍርሃት የሚኖርበት አይደለም። በሰለጠነውም፣ ባልሰለጠነውም አገር፥ ዲሞክራሲ አለ በሚባልበትም ሆነ በሌለበት አገር ፍርሃት አለ። በሥልጣኔም ሆነ በዲሞክራሲ ቀደምትነት ባለው አገር በአሜሪካም ፍርሃት አለ። ለምሳሌ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የሚሄድበት ሊንከን ሊሙዚን የተባለው መኪና አምስት መቶ ሺ ዶላር የሚያወጣ ሲሆን፥ መኪናው መለስተኛ የጦር ኃይል ሊያደርስበት የሚችለውን ጉዳት መቋቋም እንዲችል 30 ካሊበር ጥይት ቢመታው በጅ እንዳይል ሆኖ የተሠራ ነው። የመስኮቶቹ መስታወት የአየር ኃይል ተዋጊ አይሮፕላን ያለውን ዓይነት መስታወት ነው። አራቱ የጎማ ተሻካሚዎች በልዩ ብረት የተሠሩ ሲሆን፤ አራቱም ጎማዎች በአንድ ጊዜ ቢፈነዱ፥ መኪናው በቸርኬው ብቻ በከፍተኛ ፍጥነት እየተነዳ ከሃምሣ ማይል በላይ መሄድ ይችላል። ይሄ ሁሉ የመከላከያ ዘዴ የተዘጋጀው፥ ሰዎች በፕሬዚዳንቱ ላይ አደጋ ይጥሉ ይሆናል በሚል ፍርሃት ነው።*

*ሰዎች ስንባል ከአሸናፊ የሕይወት ታሪክ ውጪ ሌላ ታሪክ መስማት አንፈልግም። መስማት ብቻ ሳይሆን ያ ታሪክ የእኛ ታሪክ እንዲሆን እንፈልጋለን። ነገር ግን ሁኔታዎች እኛ እንደጠበቅናቸውና በመሆን ፈንታ፥ ያልጠበቅነው ሁኔታ ሲደርስብን እኛን ወደ በጎ አቅጣጫ የመለወጥ፣ በሕይወታችን የማሳደግ ኃይል አላቸው። ከምቾት ሕይወት ይልቅ በትግል ሕይወት ውስጥ ይበልጥ እናድጋለን። አንዳንድ ክርስቲያኖች "ሆነልኝ፤ ተደረገልኝ" በሚል ታሪክ ውስጥ መኖርን ይመርጣሉ። "ጠንካራ እምነት ቢኖርህ፥ ለእኔ የሰጠኝን ድል ወይንም ተዓምር ለአንተም ይስጥህ ነበር" በማለት የድል ታሪክ ብቻ ማውራት ይወዳሉ። "በመከራ ውስጥ ያለፈ፣ የተሰቃየ አማኝ አለ" ብለው ማውራትን አይወዱም። አማኞች ከመቶ አሥሮቹ ያለሙከራ፣ ያለችግር፣ ያለማጣት ሊያልፉ ይችሉ ይሆናል። ዘጠና ከመቶዎቹ ግን የአበባ ምንጣፍ በተነጠፈበት ሕይወት ውስጥ አያልፉም። ይህም ማለት ከመጀመሪያዎቹ እነዚህ ያነሱ ወይንም የቀዘቀዙ ክርስቲያኖች ናቸው ማለት አይደለም።*

..............................................................................................

**በሚቀጥለው ክፍል እስክንገናኝ፥ የጌታ ጸጋና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን።**